በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ሰሙነ ሕማማት - ያለንበት ሳምንት …

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# ባሃይ፤ ሂንዱይዝም፤ ቡድሂዝም

# ክፍል ዘጠኝ

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዝያ ፯ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.

# ሰሙነ ሕማማት

- ከትንሳኤ በፊት ያለው ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ቃሉ ሐመ፡ ታመመ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን ሳምንቱ የጌታችን ሕማሙና ሞቱ ይዘከርበታል።
- በተጨማሪም ከአዳም እስከ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሉ ነፍሳት በሲኦል የቆዩበት 5500 የመከራ፡ የፍዳና የኩነኔ ዘመን ስለሚታሰብበት የሕማማት ሳምንት የሚለውን ስያሜ አግኝቷል። ይህ ሳምንት ቅዱስ፤ የመጨረሻ ሳምንትም ተብሎ ይጠራል።
- በዚህ ሳምንት ኦርቶዶክሳውያን በሙሉ በጠዋት፤ በሦስት፤ በስድስት፤ በዘጠኝና በአሥራ አንድ ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማማተ መስቀል ከሚዘክሩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች በማንበብና በመጸለይ ሕማሙንና ሞቱን ይዘክራሉ። በቅዱስ ያሬድ ለዚህ ሳምንት የተዘጋጀውን መዝሙርም በመዘመር አብዝተው ይሰግዳሉ።
- በዚህ ሳምንት ከጸሎተ ሐሙስ በስተቀር ቅዳሴ አይቀደስም፤ ስብሐተ ነግህ አይደረስም፤ ጸሎተ ፍትሐትና አስተስርዮም አይደረግም፤ ጥምቀተ ክርስትናም አይፈጸምም። እነዚህ የተዘረዘሩት በሙሉ ስለዚህ ሳምንት በዕለተ ሆሳዕና ይፈጸማሉ።
- ክብረ በዓልም በዚህ ሳምንት ቢውል ከትንሣኤ በኋላ እንዲከበር ይተላለፋል።
- #… በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። … ; እንዳለው <u>ኢሳይያስ 53 3-12።</u>

# *የሰሙነ ሕማማት ዕለታት*

*እሑድ - ሆሳዕና*

- እባክህ አሁን አድን *መዝ 117፡25-26* ማለት ሲሆን ጌታችን በአህያይቱና በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ሕፃናት #ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም…;*ማቴ 21፡9* በማለት የዘመሩበት ዕለት ነው፡፡
- ስያሜውንም ያገኘው በዕለቱ ከተዘመረው መዝሙር ነው፡፡
- የጸበርት እሁድ (Palm Sunday) ይባላል፡፡ *ማቴ 21፡8*፡፡
- በዚህ ዕለት አምላካችን በድንጋዮችም ተመስግኗል፡፡ *ሉቃስ 19፡28-40፤ ዘካ. 9፡9፡፡*

*ሰኞ*

- ጌታችን በዚህ ዕለት ከቅጠል ብቻ በቀር ፍሬ ያልተገኘባትን ዕፀ በለስ ረግሟል፡፡ *ማቴ 21፡12-17፤ ማር 11፡17፤ ሉቃ 19፡45-46፡፡* ይህም እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን የሃይማኖት ፍሬ ምግባር ማጣቱን የሚያስተምረን ነው፡፡

*ማክሰኞ*

- በካህናትና በሕዝብ አለቆች #በምን ሥልጣንህ ይኸን ታደርጋለህ; ተብሎ የተጠየቀበት ነው፡፡ *ማቴ 21፡23-25፤ ማር 11፡27፤ ሉቃ 20፡1-8፡፡* መንግስታችንን ይቃወማል ብለው ለማጋጨት ለቀየሱት ስልት ጌታችንም በአምላክነቱ መልስ የማይሰጡበትን ጥያቄ ጠይቆ መልሶላቸዋል፡፡ *ማቴ 21፡25፡፡*
- ዛሬም ቢሆን መልካም ሥራን በሠራን ጊዜ ልዩ ልዩ ወገኖች እንቅፋት ሊሆኑ እንደሚችሉ ለቅን አሳባችን ከዓለም የተገላቢጦሽ መልስ እንደሚሰጠን #ዓለም የሚወድደው የገዛ ወገኑን; *ዮሐ 15፡19፡፡* እንደሆነ አሳልፈው ሊሰጡን የሚወድዱም ተፈታታኝ ጥያቄ እንደሚያቀርቡልን ያስተማረባት ዕለት ናት፡፡

# የሰሙነ ሕማማት ዕለታት…

## ረቡዕ

- የካህናት አለቆች፣ የሕዝብ ሽማግሌዎችና ጸሐፍት ፈሪሳውያን በጌታችን ላይ ተማክረዋል ይሙት በቃ ብለውም ፈርደውበታል፣ ጌታችን በስምዖን ዘለምጽ ቤት ሳለ አንዲት ከኃጢአትዋ የተጸጸተች ሴት ሽቶ ቀብታዋለች፣ ይሁዳ ጌታችንን አሳልፎ ለመስጠት ከፈሪሳውያንና ከካህናት አለቆች 30 ብር ተመዝኖለታል። *ማቴ 26፡3-16፣ ማቴ 26፡24፣ ማር 14፡1-11፣ ሉቃ 22፡1-6።*

## ኀሙስ

- ኅብስቱንና ወይኑን በባረከ ጊዜ፣ በጌቴሴማኒም ስለጸለየ ጸሎተ ሐሙስ ይባላል።
- በዚህ ዕለት የፋሲካ ዝግጅት ተደረገ፣ ጌታችን ሥርዓተ ቁርባንን ሠራ፣ ጌታችን ጸለየ፣ ይሁዳ አሳልፎ ሰጥቶት ወታደሮች ያዙት፣ ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ፣ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የማጠቃለያ ትምህርት አስተማረ። *ማቴ 26፡11-46፣ ማር 14፡12-52፣ ሉቃ 22፡1-53፣ ዮሐ 18፡1-12፣ ዮሐ 13፡4-17፣ ዮሐ 14፡16፣ ዮሐ 16፡16-22*።
- የተደረገውንም ለማሰብ ካህናት የምዕመናንን እግር ያጥባሉ፣ ከእህልም ጥንት በእስራኤል እንደነበረው በነጻነታችን ዋዜማ ለጾም ወቅት ተስማሚ የሆነውን መርጠን ባቄላ እህል ቀላቅለን እንመገባለን። *ኢያሱ 5፡11፣ 2ኛ ሳሙ 17፡28-29።*

## ዓርብ

- ጌታችን ለዓለም ድኅነት በመስቀል ላይ የዋለበት ዕለት ነው።
- ጌታችን ወደ መቃብር እስኪወርድ ድረስ
    - በሃይማኖት በሊቀ ካህናቱ ፊት ከሰሱት
    - በፖለቲካ ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጥተው በሐሰት ከሰሱት

## የሰሙነ ሕማማት ዕለታት...

- ጲላጦስ ወደ ገሊላ ገዥ ወደ ሄሮድስ ልኮት ተጠየቀ
- ሄሮድስም ንቆ ወደ ጲላጦስ መልሶት ጲላጦስ መረመረው
- ጲላጦስ በርባን ተፈትቶ ኢየሱስ ግን ተገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ
- ፕራይቶሪዮን በሚባለው ግቢ ቀይ ልብስ አልብሰው፣ የእሾህ አክሊል ደፍተው፣ ዘንግ አስይዘው ዘበቱበት
- መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወሰዱት
- በስድስት ሰዓት በጎልጎታ (ቀራንዮ- የራስ ቅል) ቸንክረው ሰቀሉት
- ልብሱን ለአራት ተከፋፈሉት፣ በእጀ ጠባቡም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ
- በመስቀል ላይ ሳለ ሰደቡት፣ ተፉበት ሆምጣጤም አጠጡት ጎኑንም በጦር ወጉት
- ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓትም በመስቀል ቆይቶ በመጨረሻ ነፍሱን ስለሁላችን አሳልፎ ሰጠ
- ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ በአዲስ መቃብር ቀበሩት

- *ማቴ 26፡37፣ ማቴ 27፡61፣ ማር 14፡53፣ ማር 15፡45፣ ሉቃ 22፡54-56፣ዮሐ 18፡12-42፡፡*

## *አሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል*

- ተኮርኦተ ርዕስ (ራሱን መመታቱ)፣ አክሊለ ሦክ (የእሾህ አክሊል መድፋቱ)፣ ተአስሮተ ድኅሪት (የኋሊት መታሰሩ)፣ ሰትየ ሐሞት(ሐሞትና ከርቤ መጠጣቱ)፣ ቅንዋተ መስቀል (ዳናት፣ አዴራ፣ ሳዶር፣አላዶር፣ ሮዳስ)፣ ተቀስፎ ዘባን (ጀርባውን መመታቱ)፣ ርግዘተ ገቦ (ጎኑን መወጋቱ)፣ ተጸፍዖ መልታህት (ፊቱን መመታቱ)፣ ተአርቆተ ልብስ (ልብሱን መገፈፉ)፣ ወሪቀ ምራቅ (ምራቅ ተፉበት)፣ ጾዊረ መስቀል (መስቀል መሸከሙ)፣ ተከይዶ በእግረ አይሁድ (በአይሁድ እግር መረገጡ፣ ወሪደ መቃብር (ወደ መቃብር መውረዱ)፡፡

## የሰሙነ ሕማማት ዕለታት...

- ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በመስቀል ላይ ሳለ ሰባት ተአምራት ተደርገዋል። ፀሐይ ጨለመች፤ ጨረቃ ደም ሆነች፤ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር ተናወጠች፤ ዓለቶች ተሰነጣጠቁ፤ መቃብራት ተከፈቱ፤ ሙታን ተነሡ። *ማቴ 27፡45-64።*
- ጌታችን በመስቀል ሳለ ሰባት የፍቅር ቃላትን ተናግ[ል። አነርሱም አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፤ እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ፤ እነኋት እናትህ እነሆ ልጅሽ፤ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ፤ ተጠማሁ፤ አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፤ ተፈጸመ።
- በዚህም ዕለት በሰሙነ ሕማማት የተሠራውን ኃጢአት ካህናት የጌታችንን መገረፍ ለማሰብ በቅጠል እየጠበጠቡ ምዕመናንን እንዲሰግዱ ያዛሉ።

### ቅዳሜ - ቀዳም ስዑር

- የድኅነት ሥራውን ፈጽሞ በከርሰ መቃብር አርፏል። በመጾማችንም የተነሣ ቀዳም ስዑር ይባላል።
- በአዳም ስህተት ምክንያት የገነት ደጅ በጌታችን ቤዛነት ተከፍቷል፤ ጥንተ ርስታችን ተመልሳልናለች፤ አባታችን አዳምም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀልን ስንል #ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ወበትንሣኤሁ አግሃደ; በማለት በኖኅ ዘመን የተላከች ርግብ ውሃው እንደጎደለ ለማብሰር ቅጠል ይዛ መጥታለችና ቀሳውስትና ዲያቆናት እየዞሩ ቄጠማ ይሰጣሉ። *ዘፍጥ 8፡11።*
- ሐዋርያት ጌታችን ከተያዘ ጀምሮ አልበሉምና የሚቻላቸው ሁሉ ያከፍላሉ። *ማቴ 9፡15*

# ባሃይ (Bahai)

- ግንቦት 22 1844 ዓ.ም. በኢራን ሺራዝ ከተማ በወቅቱ በሺያት እስልምና ተከታዮች መካከል ተከስቶ በነበረው ክፍፍል የተነሳ በመሐመድ አሊ (ባብ)፤ በመቀጠልም በበሁሴን አሊ ኑር (ባሃኡላህ) ተመሰረተ። መሰረተ ሃሳቡም በእስልምና ላይ የተገነባ ነው።

## አጠቃላይ ይዘቱ

- ራሱን ከሌሎች ሳይለይ ሁሉንም እናቅፋለን ወደፊትም ሁሉም ወደ አንድ አቅጣጫ ያመራሉ በመጨረሻም አንድ ሃይማኖት ብ ቻ ይኖራል ይላሉ። ኖኅ፤ አብርሃም፤ ሙሴ፤ ቡድሃ፤ ኢየሱስ፤ መሐመድ፤ ባብ እና ባአሁላ በቅደም ተከተል የተላኩ መልእክተኞች ናቸው ከማለት በተጨማሪ ጥቅሶቻቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ፤ ከቁርዓን በተጨማሪ ከሌሎቻችም እንቀበላቸዋለን ከሚሉት መጻሕፍትም ያነባሉ።
- ፓለቲካንም በተመለከተ አንድ የኣለም ፓርላማ ተቋቁሞ ሕግ አውጪ፤ ሕግ አስፈጻሚና፤ የፍትሕ አካላት ይደረጋሉ። የመጨረሻውም ባለሥላጣን ዓለም አቀፍ ቤተ - ፍትሕ (Universal House of Justice) ነው ይህም መቀመጫው በሐይፋ እስራኤል ይገኛል፤ ወደፊትም አንድ የዓለም አስተዳደር፤ አንድ ቋንቋ ይፈጠራል ይህንም ለውጥ በሰላማዊ ትግል ብቻ እናመጣለን ይላሉ።
- በኢኮኖሚም ለሁሉም የሚያገለግል አንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ትግል- ፉክክር- ትንቅንቅ ሁሉ ይቀራል፤ ደሃና ሀብታም ይኖራሉ ባለሀብትም መከበር ይኖርበታል፤ መሥራት ሲችል ቁጭ ብሎ የሚበላ በልመናም የሚኖር የተጠሉ ናቸው ወወላሉ።
- ማኅበራዊ ሕይወትንም በተመለከተ የእምነት አንድነትን ለማስከበር ሲባል የአንድነት ቃልኪዳናችንን ከማያከብሩ ጋር ምንም ዓይነት ማኅበራዊ ግኑኝነት እንዳያደርግ ነቢዩ ባሃኡላህ ራሱ ደንግጓል።
- ከሞት በኋላ ገነትና ሲኦል ቀጥሎም ገሃነም አለ በሚለው ትምህርት አያምኑም። ባሃኡላህም አርጓል ፤ እግዚአብሔርም አንድ አካል ነው ብለው ያምናሉ። <u>ዮሐ 3፡13፤ ማቴ 25፡32-46፡፤ ማቴ 28፡19፡</u>
- የራሳቸው የዘመን መቁጠሪያ ያላቸው ሲሆን 19 ወራትና 19 ቀናትን እያደረገ ይቆጥራሉ። የዘመን መለወጫቸውም ማርች ፳፪ ቀን ነው።
- በዓለም አቀፍ ተቋማት በUN (UNICEF, UNEP, …) ያማካሪነት ቦታ ያላቸው ሲሆኑ በኒውዮርክ፤ ጄኔቫ፤ አአ፤ ባንኮክ፤ ናይሮቢ፤ ሮም፤ ሳንቲያጎ፤ እና ቪየና ቢሮዎች አሉአቸው። በ200 አገሮች ይገኛሉ።

# <u>*ሂንዱይዝም (Hinduism)*</u>

- በተለያዩ ባሕሎችና ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዞ የተፈጠረ ስለሆነ በብቸኝነት የሚታወቅ መሥራች የለውም፡፡ ሂንዱ በጥንታዊቱ ኢራን የሚገኝ ወንዝ ስም ነው፡፡ እነዚህ በላሞች ያመልካሉ፡፡

<u>*አጠቃላይ ይዘቱ*</u>

- የሰውን ዘር በአራት ይከፍላሉ፡፡ እነርሱንም <u>ብራህማ፣ ሻትሪያ፣ ቫዚያና ሱድራ</u> በማለት ይከፍላሉ፡፡
  1. የብራህማ መደብ የሆኑት ሰዎች ቀሳውስት፣ የተማሩ፣ የሚያስተምሩ፣ ምርጥ የእግዚአብሔር ፍጡሮች ናቸው ሲሉ ዓለምም ለነርሱ ድሎት ተፈጠረች እንዳያጡና እንዳይቸገሩም አምላክ አዟል ይላሉ፡፡
  2. ሻትሪያ ጦረኛ ወገን ነው ሲሉ መሳፍንት፣ነገሥታት እና ቤተሰቦቻቸው ጨዋ ሆነው ሰውን የማስተዳደር፣ አገርን የመግዛት፣ ጦርነትን ተዋግቶ የማሸነፍ፣ ሕግንና ሥርዓትን የማስፈን ኃላፊነትና መብት ተሰጥቷቸዋል ይላሉ፡፡
  3. ቫዚያ የተባሉት ደግሞ ኑሮአቸውን በግብርና፣ በንግድ፣ በከብት ርቢ እና በጥበቃ የሚመሩ ተራ ሰዎች ናቸው ይላሉ፡፡
  4. ሱድራ የተባሉት ግን አገልጋዮች ናቸው፡፡ እነዚህን የነካ ሰው ይረክሳል፣ የእነሱን ምግብና መጠጥ መቀበልም ያረክሳል፣ አስጸያፊ ናቸው፣ ከእነርሱ ጋር መቀመጥ፣ መጓጓዝ፣ መመገብ፣ መነካካት… ክልክል ነው ይላሉ፡፡ ተከታዮቹም ወደ 781 ሚሊዮን ይጠጋሉ፡፡
- በነርሱ እምነት አምላካቸው በየጊዜው የሚለዋወጥ ሲሆን አሁንም ክሪሽና፣ ራማ ሺቫ የተባሉ አምላኮች አሉአቸው፡፡ እነርሱም ዓለምን የማስተዳደርና የመቅጣት ሥላጣን አላቸው፡፡ እነርሱም ትልልቅ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን መቆጣጠር እንጂ በየጎጆው እየገቡ የእያንዳንዱን ራስ ምታት የማዳመጥ ፍላጎት የላቸውም… የሁሉም ጠቅላይ ገዢም እግዚአብሔር ነው ይላሉ፡፡ ሰው ሲሞት አስከሮኔ ይቃጠላል፡፡
- ከአምላኮቻቸውም በታች በሥልጣን ተዋረድ ኡቃቢ፣ አቴቴ፣ አድባርን የመሳሰሉ አሉ፡፡ እነዚህም የድሆችን ችግር፣ የበተሰብን ጉዳይ በየመንደሩ ቅርብ ሆነው ዘወትር የሚከታተሉና የሚጠብቁ እንዲሁም በበሽታ የሚቀጡ ናቸው ተብለው ይታመናሉ፡፡ ክሪሽናን እንደ መድኃኔዓለም ይቆጥሩታል፡፡
- ሰው ሲሞት ነፍሱ ወጥታ በሕይወቱ ከሰራቸው ሥራዎች ወደ ሚመስለው አካል ትገባለች፣ እንደጥፋቱም መጠን በእንስሳ መልክም ከተወለደ በኋላ ሰው እንዲሆን ዕድል ይሰጠዋል ይላሉ፡፡
- ዮጋ የሂንዱ አንዱ ክፍል ሲሆን መንፈስን ከዓለማዊ ፍላጎት ማላቀቂያ ፍልስፍናቸው ነው፡፡

# ቡድሂዝም (Buddhism)

- በዛሬዋ ኔፓል የሂማልያ ተራራ ግርጌ በተወለደው ጉተማ ቡድሃ የተመሰረተ የልምምድ፤ የአስተሳሰብና የ#ሃይማኖት; ስብስብ ነው፡፡
- ቡድሃ በአራት ክፍሎች የተጠቃለሉ ትምህርቶች አስተማረ በአጭር ጊዜ ውስጥም እስከ ሃምሳ የሚደርሱ ተከታዮችን አፈራ፡፡ ለ45 ዓመታትም አስተምሮ በ400 ከክ.ል.በ ሞተ ይላሉ፡፡

*አጠቃላይ ይዘቱ*

- አትግደል፤ የራስህ ያልሆነውን አትውሰድ፤ የሰው ሚስተ አትሻ፤ አትዋሽ፤ የሚያሰክር መጠጥ አትውሰድ የሚል ሕግ ቡድሃ ደንግጓል፡፡
- በቡድሃ አስተምህሮ ሰው ከኃጢአቱ የሚነጻው በራሱና በራሱ ጥረት ብቻ ነበረ፡፡ ከጊዜ በኂላ ሰዎች እየከበዳቸው ሲሄድ የሚያቀልላቸው መንገድ ፈልገው ቡድሃን ከተራ አስተማሪነት ወደ አምላክነት አሸጋገሩት፡፡
- በቡድሃ እምነት መንግሥተ ሰማያት ገዢዋ ታላቁ አሜታባ ሲሆን ምድርንም የፈጠረው አዲ ቡድሃ ነው ይባላል፡፡ ሌሎችም ብዙ ቡድሃዎች አሉ ብለው ያምናሉ፡፡
- በቡድሃ ሌሎች የጥንቆላና የመተት ድርጊቶች ጨምረውበታል፡፡ መናፍስትን መሳብ፤ ድግምትን መድገም፤ ክታብ በመጻፍ ከበሽታ መፈወስ … የሚሉ መንገዶችንም አመቻችተዋል፡፡
- ቪናያ የሚባል የሞራል መመሪያ አዘጋጅተው ወንዶችም ሴቶችም በምንኩስና እንዲኖሩ ያስተምራሉ፡፡ መነኮሳቱም ሥጋ እንዳይመገቡ በሕግ ይከለከላሉ፡፡ ጃፓን ምንኩስናን ፈጽሞ በመከልከል የቡድሃ አገልጋዮች እንዲያገቡ ታስገድዳለች፡፡
- ቡዲዝም በተለያየ መልኩም ቢሆን በከፊል ሕንድ፤ በደቡብ ምስራቅ እስያ፤ በቻይና ይታመንበታል፡፡
- የዚህ ተከታዮች ወደ 324 ሚሊዮን ይጠጋሉ፡፡

# እምነትና ሥራ - …

## ማጠቃለያ…

ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም ያድርሰን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።